የአብዱል-ባሃ ፀሎቶች



የአብዱል-ባሃ ፀሎቶች

ማርች 2021

1

እርሱ አምላክ ነው።

አቤቱ እናንተ የመንግሥተ ሰማያዊ ሠራዊት በዙሪያዋ የሚሽከረከሩባት ሥፍራ በአምልኮ የምትዞሩት ሆይ! በምስጋና በአንዱ እውነተኛ አምላክ ደጃፍ እጆቻችሁን ከፍ አድርጋችሁ በመዘርጋት፣ እንዲህ በሉ፡— አንተ የእያንዳንዱ ጽኑ አፍቃሪ እጅግ ከፍተኛው እሾት ሆይ! አንተ የእያንዳንዱ ተንከራታች ነፍስ መሪው ሆይ! ይህንን ደካማ አገልጋይ በአንተ ወሰን አልባ ቡራኬዎች አጎናጸፍከው፣ ይህንን ምስኪንና ዝቅተኛውን ወደ አንተ አንድነትህ ደጀሰላም መራኸው፡፡ ለእነዚህ ለደረቁ ከናፍር የአፍቃሪ ደግነትህን የሕይወት ውሃዎች አጎልብትክላቸው ይህንንም የዛለና የጠወለገ ነፍስ በመለኮታዊ ምህረት ልዝብ ነፋሶች ሕይወት ዘራህበት። ከእጅግ በጣም ጸጋ ከተመላ ችሮታህ ሙሉ ድርሻ ስላጎናጸፍከኝ ወደ ቅድስናህም መንበር [1] የመቅረብን ክብር ስለሰጠኸኝ ምስጋና አቀርባለሁ። ከላይኛው መንግሥትህ ችሮታዎች ወሰን አልባ ድርሻ እማጠንሃለሁ። እርዳታህን ስጠኝ፡፡ ጸጋ የተመላ ችሮታህን ለግሰኝ፡፡

[1] *የባሃኣላህ መካነ-መቃብር*

2

አቤቱ አንተ የማትታየው ወዳጄ ሆይ! በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም ያሉት ሁሉ እሾት ሆይ! አንተ ሩህሩሁ ተወዳጁ ሆይ! እነዚህ ረዳት የለሽ ነፍሶች በአንተ ፍቅር ተማርከዋል፣ እነዚህም ደካሞች በአንተ ደጀሰላም መጠለያ ፈልገዋል። በእያንዳንዱ ምሽት ከአንተ በመራቃቸው ይቃትታሉ ያቃስታሉም፥ በእያንዳንዱም ንጋት በከፉ ሕዝቦች ጥቃት ምክንያት ያዝናሉ ያለቅሳሉም። በእያንዳንዱ ቅፅበት በአዳዲስ ጭንቀቶች እየተሰቃዩ ናቸው፣ በእያንዳንዱ ክፉ አድራጊ ጨቋኝ ጭካኔ በየአንዳንዱ እስትንፋሳቸው-በከባድ ተፈትነዋል። ላንተ ምስጋና ይድረስህይህንን ተቋቁመው፣ እንደ እሣት መቅደስ ደምቀው በመንደድ እንደ ፀሐይና ጨረቃ በአንፀባራቂነት በርተዋል። በአምላክ እምነት ውስጥ፣ ተሰቅሎ እንደሚውለበለብ ሠንደቅ፣ ቀጥ ብለው ቆመው፣ እንደ ጀግኖች ፈረስ ጋላቢዎች፣ ወደ ውጊያው መስክ እየተጣደፉ ናቸው።
እንደ ጣፋጭ አበቦች ፈክተዋል እንደሚፍነከነክ ጽጌረዳም በደስታ ተሞልተዋል። አንተ አፍቃሪው ሰጪው ሆይ፣ እነዚህን ቅዱሳን ነፍሶች በፀጋህ እረድተህ ከአንተ መንግስት የሚቸረውን የአንተን ሰማያዊ ቡራኬ አጎናፅፋቸው፣ እነዚህም የተቀደሱ ስብዕናዎች የእጅግ ከፍተኛውን ምልክቶች መግለጽ እንዲችሉ አድላቸው።

አንተ ፍጹም ለጋሱ፣ አዛኙ፣ ፍጹም መሃሪው፣ ሩህሩህ ነህና።

3

አቤቱ አንተ ተወዳዳሪ የሌለህና አፍቃሪ ጌታ ሆይ! ችሎታና እርባና ቢጎድሉም፣ እንዲሁም መከራን መቋቋምም ከመጠን በላይ አዳጋች ቢሆንም፣ ነገር ግን እርባና እና ችሎታ ከአንተ የሚጎናጸፉት ስጦታዎች ናቸው። ጌታዬ ሆይ! ምናልባት እጅግ ታላቅ ጽናትን ለማሳየት እንችል ዘንድ፣ ይህችን ዓለምና መላውን ሕዝቧን እንድንተው፣ የፍቅርህን እሳት አቀጣጥል፣ እንደሻማዎችም በሚጨርስ ነበልባል በድምቀት እንድንነድ ብርሃናችንም በስፋት እንዲናኝ ችሎታን ስጠን እርባና ያለንም አድርገን።

የመንግሥቱ ጌታ ሆይ! ከዚህ ዓለም ባዶ ቅዠቶች አላቀን፣ ወደ ወሰን አልባው ግዛትህም ምራን። ከዚህ ዝቅተኛ ዓለም ሙሉለሙሉ እንድንላቀቅ ፍቀድልን፣ በመንግሥቱ ጸጋ የተመሉ ስጦታዎች እንድንባረክ አድርገን። እውናዊ መስሎ ከሚታየው ከዚህ ምንምነት ዓለም አላቀህ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትን አጎናፅፈን፡ ፡ ሐሴትንና ደስታን ስጠን፣ እንዲሁም ደስተኝነትና እርካታ አድለን። ወደ መንግሥትህ ስናርግ ቅርበትህን

እንድንቀዳጅና በላይኛው ግዛቶች እንደሰት ዘንድ፥ ልቦቻችንን አጽናናልን፥ ለነፍሶቻችንም ሰላምና እርጋታን አድለን። አንተ ሰጪው፥ ለጋሱ፥ እና ኃያሉ ነህና።

4

ዘለዓለማዊ ተፈቃሪዬና ተወዳጅ ጓደኛዬ ሆይ! ከቅርበትህ ተነፍጌ እና ከአንተ በመራቅ በጽኑ ተጎድቼ የምቆየው ለምን ያህል ጊዜ ነው? ወደ መንግሥተ ሰማያዊ ግዛትህ መሸሸጊያዎች ስፍራዎች ምራኝ፥ እንዲሁም የመለኮታዊ ግዛትህ መታያ መድረክ ላይ የፍቅራዊ ደግነትህን ቅጽበታዊ ዕይታ አሳርፍብኝ።

አንተ ምንም የማይሳነው ጌታ ሆይ! ከመንግሥትህ ነዋሪዎች መካከል ቁጠረኝ። ይህ ጠፊ ዓለም መኖሪያ ሥፍራዬ ነው፤ በሥፍራ አልባ ግዛቶችህ ውስጥ መኖሪያ ሥፍራ ስጠኝ። የዚህ ምድራዊ ሥፍራ አካል ነኝ፤ የተከበረው ብርሃንህን ነጸብራቅ በላዬ አፍስልኝ። በዚህ የአቧራ ዓለም ውስጥ እኖራለሁ፤ ምናልባት በመንገድህ ሕይወቴን አሳልፌ በመስጠት የልቤን እሾት ለመቀዳጀት እንድችል፥ በመለኮታዊ ችሮታ አክሊል በራሴ ላይ እንድደፋ እና " እጅግ ንዑዱ፥ የአምላክ ክብር ሆይ!" የሚለውን የድል ደስታ ጩኸት ከፍ እንዳደርግ የመንግሥተ ሰማያዊው ግዛት ባለሟል አድርገኝ።

5

አቤቱ አንተ ቸሩ ጌታ ሆይ! እነዚህ ነፍሳት በጋራ የተሰባሰቡ እና በፍቅርህ የተነሳሱ ወዳጆችህ ናቸው። በአንተ ውበት ጨረሮች ከፍ ብለው፣ በዝባድ ውህድ በተነነነነ ጸጉርህም ተማርከዋል። ልቦቻቸው ለአንተ እጅ ሰጥተዋል፣ ዝቅተኞቹ እና ረዳት የለሾቹ በአንተ መንገድ ተንከራተዋል ። ወዳጅም ሆነ ባይተዋር ሁሉንም ትተዋል በፊትህ በማክበር አጎንብሰው አንድነትህንም አጥብቀው ይዘዋል።

የዚህ ዝቅተኛ ዓለም አካል ነበሩ፤ ወደ መንግሥትህ ጠራሃቸው። በመነፈግና እጦት ዱር ውስጥ እንደጠወለጉ ዕጽዋት ነበሩ፤ የዕውቀትና መረዳት አትክልት ሥፍራ ቡቃያዎች አደርግሃቸው። ድምጽ አልባ ተደርገው ነበር፤ እንዲናገሩ አደረግሃቸው። ተስፋ ቆርጠው ነበር፤ የሚያነቃቃ ብርሃን በላያቸው አፈሰስክ። እንደደረቀና ጠፍ መሬት ነበሩ፤ ወደ ውስጣዊ ትርጉሞ ወዳለው የጽጌረዳ አትክልት ሥፍራ ለወጥካቸው። በሰው ዘር ዓለም ውስጥ እንድ ልጆች ነበሩ፤ መንግሥተ ሰማያዊ ብስለት እንዲቀዳጁ አስቻልካቸው።

አቤቱ አንተ ሩህሩሁ ሆይ! በአንተ ጥበቃ መጠለያ ገነት ውስጥ ከለላን ስጣቸው፣ ከፈተናዎችና

መከራዎች ጋርዳቸው፡፡ የአንተን የማይታየውን እርዳታህን አውሳቸው፣ የአንተንም የማይሳሳተውን ፀጋ አጎናፅፋቸው፡፡

አንተ ደግና ተወዳጅ ጌታ ሆይ! እነርሱ ልክ እንደ አካል ናቸው፥ አንተ ደግሞ የሕይወት መንፈስ ነህ። የአካል አዲስነትና ውበት በመንፈስ ጸጋ ላይ የተመረኮዘ ነው። ስለዚህ፥ በዚህ አዲስ ግልጸት ማረጋገጫዎችህን በመፈለግ እና የመንፈስ ቅዱስ ደጋፊ ኃይል በመሻት ይጸናሉ። አንተ ኃያሉ ነህ። አንተ ሰጪው፥ ቸሩ፥ ሊጋሱ፥ እንዲሁም ይቀርባዩ ነህና። አንተ ከማይታየው ግዛት በድምቀት የሚየበራው ነህ።

6

መለኮታዊ ሰጪ ሆይ! ግራ የሚያጋቡ ችግሮች ተነስተዋል አዳጋች መሰናክሎችም ብቅ ብለዋል። ጌታ ሆይ! እነዚህን ችግሮች አስወግዳቸው እንዲሁም የኃይልና ሥልጣንህን ማረጋገጫዎች አሳይ። በዚህ ፈታኝ ጎዳና እነዚህን መከራዎች አቅልላቸው መንገዳችንንም አለዝብልን። መለኮታዊ ሰጪ ሆይ! መሰናክሎቹ የማይበገሩ ናቸው፥ እንዲሁም ልፋቶቻችንና ችግሮቻችን ቁጥር ስፍር ከሌላቸው መከራዎች ጋር ተጣምረዋል። ከአንተ በቀር ሌላ አጋዥ የለም፥ ከአንተም በቀር ሌላ ረዳት የለም።

መላ ተስፋችንን ባንተ ላይ አድርገናል፥ መላ ጉዳያችንንም ላንተ ጥበቃ ትተናል። አንተ መሪውና የእያንዳንዱ ፈተና አስወጋጁ ነህ፥ እንዲሁም አንተ ጠቢቡ፥ ተመልካቹ፣ እና ሰሚው ነህ።

7

የምህረት አምላክ ሆይ! አንተ ምንም የማይሳነው ሆይ! እኔ አቅመቢስ፥ ደካማና ረዳተቢስ አገልጋይ ነኝ፥ ሆኖም በጸጋህና በችሮታህ መጠለያ ውስጥ አድጊያለሁ፥ ከምህረትህ ጡት ተመግቢያለሁ፥ በፍቅራዊ ደግነትህ እቅፍም ውስጥ አድጊያለሁ። ጌታ ሆይ! ድሃና ተመጽዋች ብሆንም፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ተመጽዋች በአንተ ቸርነት አማካይነት ይበለጽጋል፥ እያንዳንዱ ባለጸጋ የአንተን ችሮታ ቢነፈግ፥ በእርግጥ ድሃና ብቸኛ ነው።

መለኮታዊ ሰጪ ሆይ! የፈተናዎች ኃይል በጣም ብርቱ ስለሆነ እና የመከራዎች ጥቃት በጣም የከፋ በመሆኑ እያንዳንዱ ተራራ በአቧራ ውስጥ እንዲበተን፥ እንዲሁም እጅግ ከፍተኞቹ የተራራ ጫፎች ወደ ምንምነት እንዲወርዱ፥ ይህን ከባድ ሸክም ለመሸከም ብርታት አድለኝ፥ ይህንንም የላቀ ስጦታ ለመጠበቅ አስችለኝ። በልቤ ውስጥ ከአንተ ትውስታ በቀር

ምንም እንደማልፈልግ፥ በነፍሴም ከአንተ ፍቅር በቀር ምንም እንደማልሻ በደንብ ታውቃለህ። ተወዳጆችህን ለማገልገል አሰልጥነኝ፥ በመንበርህም ለዘለዓለም በማገልገል እንድኖር ፍቀድልኝ። አንተ አፍቃሪው ነህ። አንተ የዘርፈ ብዙ ቸርነቶች ጌታ ነህ።

8

መለኮታዊ ሰጪ ሆይ! አንቃኝ አስተዋይም አድርገኝ። ከአንተ በቀር ከሁሉም የተላቀቅሁ አድርገኝ፥ በውበትህም ፍቅር ማርከኝ። የመንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ በላዬ አርብብብኝ፥እንዲሁም የአብሃ መንግሥትንም ጥሪ ለማድመጥ አትንፈገኝ። መንግሥተ ሰማያዊ ኃይል ለግሰኝ፥ በውስጣዊው የልቤ ክፍልም ውስጥ የመንፈስ ሻማ አቀጣጥል። ከአንተ መልካም ፈቃድ በቀር ምንም ፍላጎት እንዳያድርብኝ፥ ከአንተ ገጽታ በቀር ምንም እንዳልፈልግ፥ ከአንተም መንገድ በቀር ሌላ መንገድ እንዳልጓዝ፥ ከማንኛውም ትሥሥር ነጻ አውጣኝ ከማንኛውም ቁራኛነትም አላቀኝ። ቸልተኞቹ አስተዋይ እንዲሆኑ ያሸለቡትም እንዲነቁ ፥ ለእነዚያ በድኑ ለተጠሙት የሕይወት ውሃን ለማቅረብ እና ለእነዚያ ለታመሙትና ለበሽተኞቹ መለኮታዊ ፈውስ ማምጣትን አስችላቸው ዘንድ አድለኝ።

ምንም ያህል ዝቅተኛ፥ የተዋረድኩ፥ እና ድሃ ብሆንም አንተ ግን መጠለያዬና መሸሸጊያዬ፥ ደጋፊዬና ረዳቴ ነህ። ሁሉም በአግራሞት ይዋጡ ዘንድ እርዳታህን ላክልኝ። አምላኬ ሆይ! በርግጥ አንተ ኃያሉ፥ እጅግ ኃይል የተመላው፥ ሰጪው፥ ለጋሱ፥ እና ሁሉን ተመልካቹ ነህ።

9

እርሱ አምላክ ነው።

አምላክ ሆይ፥ አምላኬ ሆይ! ፊቴን ወዳንተ መልሻለሁ፥ የፈውስህንም ውቅያኖስ እንድታጎርፍልኝ እማጠንሃለሁ። ጌታ ሆይ፥ ሕዝብህን እንዳገለግልና አገልጋዮችህን እንድፈውስ በጸጋህ እርዳኝ። አንተ ከረዳኸኝ ለእያንዳንዱ ሕመም የፈውስ መድሐኒት፥ ለእያንዳንዱ የሚያቃጥል ጥም ሕይወት ሰጪ ውሃዎች ምንጭ፥ ለእያንዳንዱ ናፋቂ ልብም ማስታገሻ ቅባት ይሆናል። አንተ ካልረዳኸኝ፥ ከመከራ በቀር ምንም አይሆንም፥ እንዲሁም ለማንም ነፍስ ፈውስ ፈጽሞ አያመጣም።

አምላክ ሆይ፥ አምላኬ ሆይ! በኃይልህ አማካይነት የታመመውን እንድፈውስ እርዳኝ ደግፈኝም። በርግጥ

አንተ ፈዋሹ፣ አርኪው፥ እርሱ የእያንዳንዱ ስቃይና ህመም አስወጋጅ የሆንከው፥ አንተ በሁሉ ነገሮች ላይ ሥልጣን ያለው ነህና።

10

ጌታ ሆይ! የቀናቴ መጨርሻዎች ከመጀመሪያዎቹ ይበልጥ ነጥሮ እንዲለይ፥ የሕይወቴም መደምደሚያዎች ወደ ዘርፈ ብዙ ቡራኬዎችህ መግቢያ በሮችን ይከፍት ዘንድ የጸጋህንና አፍቃሪ ደግነትህን ፥ የጥበቃህንና መከታነትህን፥ የመጠለያህንና ቸርነትህን መለኪያ መጠን ለግሰኝ። ከፍ ባለው መስፈርትህ ከለላ ሰጪ ጥላ ሥር፥ በመጨረሻም ወደ ፍጹም ተወዳሹ መንግሥትህ መግባት እንድችል በእያንዳንዱ ቅጽበት የአፍቃሪ ደግነትህና ጸጋህ ይረፍብኝ፥ በእያንዳንዱ እስትንፋስ ይቅርታህንና ምህረትህን ስጠኝ። አንተ ሰጪውና ምንጊዜም አፍቃሪው ነህ፥ በእውነቱ አንተ የግርማና የጸጋ ጌታ ነህ።

11

አንተ ሰጪው ሆይ፥አንተ ይቅር ባዩ ሆይ ! የተባረከ ነፍስ ወደ እውነት መንግሥት አርጓል፥ ከምድራዊ

የአቧራ ዓለም ወደ ዘለዓለማዊ ክብር ግዛት ገስግሷል። የዚህን በቅርብ የደረሰውን እንግዳ ደረጃ ከፍ አድርግ፥ ይህን ፀንቶ የቆመ አገልጋይ በአዲስና ድንቅ መንናጸፊያ አስጊጠው።

አንተ ተወዳዳሪ የሌለህ ጌታ ሆይ! ይህ ነፍስ ወደ ምስጢሮችህ መሸሸጊያ እንዲገባ ይፈቀድለት ዘንድ እና በድምቀቶችህ ጉባኤ ወስጥ ጥብቅ ወዳጅ ይሆን ዘንድ ይቅርታህንና አፍቃሪ ክብካቤህን ለግሰው። አንተ ሰጪው፥ ለጋሱ፥ ዘለዓለም አፍቃሪው ነህ። አንተ ይቅር ባዩ፥ አፍቃሪው፥ እጅግ ኃይል የተመላው ነህ።

12

እርሱ አምላክ ነው።

አንተ ይቅር ባይ ጌታ ሆይ! እነዚህ አገልጋዮች የተባረኩ ነፍሶች ናቸው፥ እነዚህም ብሩህ ልቦች በመርሆህ ብርሃን አማካይነት እንዲያበሩና እንዲያንጸባርቁ የተደረጉ ናቸው ። የፍቅርህን ወይን ጠጅ የሞላ ጽዋ ጠጥተዋል፥ በዕውቀትህ ጥኡም ዜማዎች ለተላለፉት ዘለዓለማዊ ምስጢሮች ጆሮአቸውን አቅንተዋል። ልቦቻቸውን ላንተ አስገዝተዋል፥ ከጠላትነት ወጥመድ ነጻ አውጣቸው፥ አንድነትህንም እንዲይዙ አድርጋቸው:: እነዚህን

ከቡር ነፍሶች የገነት ነዋሪዎች ወዳጆች አድርጋቸው፥ ወደምርጦችህም ክበብ አስገባቸው። በላይኛው ግዛት መሸሸጊያዎች ውስጥ የምስጢሮችህ ባለሟል አድርጋቸው፥ በብርሃናት ባህር ውስጥ አስጥማቸው። አንተ ሰጪው፥ አንጸባራቂው ና ሩህሩሁ ነህ።

13

መለኮታዊ ሰጪው ሆይ! የዚህን የመንበርህ አገልጋይ አባትና እናት በምህረትህ ውቅያኖስ ውስጥ አስጥማቸው፥ ከእያንዳንዱም ኃጢአትና ሕግ መተላለፍ አንጻቸው ቀድሳቸውም። ይቅርታህንና ምህረትህን አድላቸው፥ ጸጋ የተመላ ሐዘኔታህን በላያቸው አውርድላቸው። በርግጥ አንተ አዛኙ፣ ዘላለም ይቅር ባዩ ፣ የተትረፈረፈ ጸጋ ሰጪው ነህ። አንተ ይቅር ባዩ ጌታ ሆይ! ሐጢአተኞች ብንሆንም እንኳ ተስፋችን በአንተ ቃልኪዳንና ዋስትና ላይ አተኩሯል። ምንም በስህተት ጨለማ ውስጥ ተጠቅልለን ብንሸፈንም እንኳን ሁሌም ጸጋ ወደተመላው ችሮታዎችህ ንጋት ፊታችንን እናዞራለን። ለመንበርህ የሚገባውን አድርግልን፥ ለደጅ-ሰላም ተገቢ የሆነውን አጎናጽፈን። አንተ ዘላለም ይቅር ባዩ፥ ምህረት አድራጊው፥ እያንዳንዱን ጉድለት የማትከታተለው ነህና።

14

አንተ ሩህሩህ ጌታ ሆይ! ልቤን ከሁሉም ቁራኛነት ቀድስልኝ፥ በምስራች ዜናዎችም ነፍሴን በሐሴት አስደስትልኝ። ከወዳጅም ሆነ ባይተዋር ቁርኝት አላቀኝ፥ ሙሉለሙሉ ለአንተ ታማኝ ለመሆን እንድችል እና በጽኑ ደስታ እንድሞላ፤ ከአንተ በቀር ምንም እንዳልሻ፥ ከአንተ በቀር ማንንም እንዳልፈልግ፥ ከአንተ በቀር በሌላ ጎዳና እንዳልጓዝ፥ ከአንተም ጋር ብቻ እንዳወጋ፤ ልክ እንደዘማሪዋ ወፍ በፍቅርህ ተገርሜ፥ በቀንና በማታ እንዳቃስት እንዳዝን እንዳለቅስና "ያ ባሃኣላህ-አብሃ!" ብዬ እንድጮህ በፍቅርህ ማርከኝ።

15

ጌታ ሆይ! ምን ዓይነት የጸጋ ነጎድጓድ ነው የለገስከው፥ ምንስ ዓይነት የተትረፈረፈ ሞገስ ጎርፍ ነው ያደልከው! ሁሉንም ልቦች እንደ አንድ ልብ እንዲሆኑ፥ ሁሉንም ነፍሶችም እንደ አንድ ነፍስ እንዲጣመሩ አደረካቸው። በድን አካላትን ሕይወት ና ስሜትን አላበስካቸው፥ በሕይወት አልባ መዋቅሮችም ላይ የመንፈስ ንቃተ-ኅሊና ለገስካቸው። ከፍጹም መኃሪው የቀኑ ኮከብ በሚፈሱት አንጸባራቂ ጨረሮች አማካይነት፥ እነዚህን የአቧራ አተሞች/ቅንጣቶች በሚታይ ህልውና

አለበስካቸው፥ በአንድዬነት ውቅያኖስ ሞገዶችም አማካይነት እነዚህ ኢምንት ጠብታዎች እንዲተሙና እንዲያጓሩ አስቻልካቸው።

የሰንበሌጥን ቀጭን ጠርዝ በተራራ ኃይል ፥ የአቧራ ቅንጣትንም የአንጸባራቂዋን ጸሃይ ክብር እንዲያንጸባርቅ የምታድለው ኃያሉ ሆይ! እምነትህን ለማገልገል መነሳት እንድንችል እና በምድር ሕዝቦች ፊት እንዳናፍር፥ ፍቅራዊ ጸጋህንና ችሮታህን ስጠን።

16

አንተ ምንም የማይሳነው ጌታ ሆይ! እኛ ሁላችንም በኃይልህ ግዙፍ መዳፍ ውስጥ ተይዘናል። አንተ ደጋፊያችን እና ረዳታችን ነህ። አፍቃሪ ምህረትህን አድለን፥ ችሮታህን ስጠን፥ የፀጋ በሮችን ክፈት፥ እንዲሁም የችሮታህን የጨረፍታ እይታ አሳርፍብን። ሕይወት ሰጪ እስትንፋስ በላያችን ያርብብን፥ ናፋቂ ልቦቻችንም አንቃልን። ዓይኖቻችንን አብራልን፥ የልቦቻችንንም መቅደስ እያንዳንዱ የሚፈካ አትክልት ከለላ የሚያስቀና ቦታ አድርገው። እያንዳንዱ ነፍስ ሐሴት ያድርግ እያንዳንዱ መንፈስም ደስታን አላብሰው። ጥንታዊው ኃይልህን ግለጽ ታላቅ ኃያልነትህንም ግለጥ። የሰው ነፍሶች ወፎች ወደ አዲስ

ከፍታዎች እንዲበሩ አድርግ፥ እንዲሁም በዚህ ዝቅተኛ ዓለም ውስጥ ታማኞችህ የመንግሥትህን ምስጢሮች ጠልቀው እንዲያውቁ አድርጋቸው። እርምጃዎቻችንን ጽኑ አድርግልን የማያወላውሉ ልቦችም አጎናጽፈን። እኛ ኃጢአተኞች ነን፥ አንተ ደግሞ ዘላለም ይቅር ባዩ ነህ። እኛ አገልጋዮችህ ነን፥ አንተ ደግሞ ሉዓላዊ ጌታ ነህ። እኛ መጠለያ አልባ ከርታቶች ነን፥ አንተ ደግሞ መሸሸጊያችንና መጠለያችን ነህ። ጣፋጭ መዓዛህን ለማሰራጨትና ቃላትህን ከፍ ለማድረግ በፀጋህ እርዳን ደግፈንም። የነዳያንን ደረጃ ከፍ አድርግ፥ ለተጎሳቆሉትም ከማያልቀው ሃብትህ ለግሳቸው። ለደካማው ጥንካሬህን ስጠው፥ ለአቅመቢሱም መንግሥተሰማያዊ ኃይል አድለው። አንተ ሰጪው ነህ፥ አንተ ባለፀጋው ነህ፥ አንተ በሁሉ ነገሮች ላይ የበላይ ጌታ ነህ።

17

እርሱ እጅግ ቅዱሱ፥ እጅግ በጣም የተከበረው ነው።

በእግዚአብሔር ስም፥ በሩህሩሁ፥ በመኃሪው! የዓለማት ሁሉ ጌታ ለሆነው ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው።

መሸሸጊያዬና መጠጊያዬ የሆንክ ጌታ አምላኬ ሆይ! በእጅግ ድንቅ የማሞካሻ ቃላትም ሆነ እጅግ ልብ

የሚነኩ የውዳሴ መድብሎች፥ አንተ ኃያሉና ይቅርባይ የሆንከው ሆይ፥ የእያንዳንዱ አንደበተ ርቱዕ ተናጋሪ አንደበት አፉ እንደሚተሳሰር፥ እያንዳንዱም ከሰው ብዕርም ሆነ አንደበት የሚገለጽ ውዳሴ የአንተን ምንም የማይሳነው ኃይል ከምልክቶችህ አንዱን ብቻ እንኳን ለማክበር ወይም በአንተ የተፈጠረችውን አንዲት ቃል ለማወደስ በሚያደርገው ሙከራ ግራ መጋባቱን እያወቅሁ፥ እንዴት በተገቢው ሁኔታ አንተን ላነሳ እችላለሁ። በእርግጥ የሰው አዕምሮዎች ወፎች ክንፎች ወደ መለኮታዊ ቅድስናህ ህዋ ለመብረር በሚያደርጉት ሙከራ ሰባራ ናቸው፥ የከንቱ ምናብ ሽረራቶችም የዕውቀትህ አኅበር እጅግ ከፍተኛ የተራራ ጫፍ ላይ ደካማ መረባቸውን ለማድራት ኃይል አልባ ናቸው። ስለዚህ ኃይል አልባነቴንና ጉድለቴን ከመቀበል ውጭ ምንም ምረጫ የለኝም፥ የድህነትና እጦት ጥልቀቶች ውስጥ በቀር ሌላ መኖሪያ ሥፍራ የለኝም። በእርግጥ አንተን ለመገንዘብ ኃይል አልባ መሆን የመረዳት ፍሬ ነገር ነው፥ ጉድለቶችን መናዘዝ የአንተን ቅርበት መቀዳጃ ብቸኛ መንገድ ነው፥ ድህነትን መቀበልም የእውነተኛ ሐብት ምንጭ ነው።

ጌታ ሆይ! ለተከበረው መንበርህ ግልጋሎታችን እኔንና ትሁታን አገልጋዮችህን በጸጋህ እርዳን፥ ለመለኮታዊ ቅድስናህ በተማጽኖአችን አበርታን፥ እንዲሁም

በአንድዬነትህ በር ፊት ዝቅተኛና ትሁት ለመሆን አስችለን። ጌታዬ ሆይ እርምጃዎቼን በመንገድህ አጽናልኝ፥ ልቤንም ከመንግሥተ ሰማያዊ ምስጢሮችህ በሚፈሱት አንጸባራቂ ጨረሮች አብራልኝ። ከምህረትህና ይቅርታህ ገነት በሚንፍሰው አነቃቂ ለስላሳ የንፋስ ሽውታ መንፈሴን አድስልኝ፥ እንዲሁም ከቅድስናህ መስኮች በተሰራጨው ሕይወት ሰጪ ልዝብ ነፋስ አማካይነት ነፍሴን አስደስት። ፊቴን ከአንድነትህ አድማስ በላይ ደማቅ አድርገው፥ እንዲሁም እንደ ትሁታን አገልጋዮችህ መታሰብ እንድችል እና ጽኑና የማያወላውሉ ሆነው ከቆሙት ገባሮችህ ጋር እንድቆጠር አድለኝ።

18

ጌታ አምላካችን ሆይ! እኛ ረዳተ ቢስ ነን፥ አንተ የብርታትና የኃይል ጌታ ነህ። እኛ ምስኪኖች ነን፥ አንተ ኃያሉ፥ ንዑዱ ነህ። እኛ ድሆች ነን፥ አንተ ሁሉም ያለው፥ እጅግ ለጋሱ ነህ። ለተቀደሰው መንበርህ ግልጋሎታችን በጸጋህ እርዳን፥ እንዲሁም በውዳሴህ የንጋት ሥፍራ አንተን እንድናመልክህ፥ በአበረታች ጸጋህ አማክይነት ደግፈን። በፍጡራንህ መካከል የአንተን ቅዱስ መዓዛ ለማሰራጨት አስችለን፥ እንዲሁም ሁሉንም አገሮች ወደ እጅግ በጣም ታላቁ ስም እንድንመራ እና ሁሉንም

ሕዝቦች ወደ አንድዬነትህ የተከበረ ውቅያኖስ ጫፎች ለመምራት እንችል ዘንድ፥ በአገልጋዮችህ መካከል አንተን እንድናገለግል ሽንጠቻችንን አጠንክርልን።
ጌታ ሆይ! በላቀ ደስታና ብሩህነት ቃላትህን ለማወደስ እንድንነሳ እና ምስጋናህን በቀንና በምሽት ወቅት ለማክበር እንችል ዘንድ፥ ሁሉንም ሰዎች ወደ መርሆ ጎዳና እንድንጠራና ቀጥተኝነትን እንዲያከብሩ ለመደንገግ እንችል ዘንድ፥ እንዲሁም በመላው ፍጥረትህ መካከል የአንድነትህን ስንኞች ማዜም እንችል ዘንድ፥ ከዓለምና ሕዝቦቿ ቁርኝት፥ ካልፉት ጊዜያት ሕግ መተላለፎች፥ ወደፊት ከሚመጡት መከራዎችም ነጻ አውጣን።
የሚያስደስትህን ለማድረግ ኃይል አለህ። በእውነቱ አንተ ሁሉን ቻዩ፥ ፍጹም ኃያሉ ነህና።

19

እርሱ አምላክ ነው።

አንተ ደግና ተወዳጅ ጌታ ሆይ! እነዚህ ወዳጆች በቃልኪዳኑ የወይን ጠጅ የተነቃቁ እና በፍቅርህ በረሃ የሚንከራተቱ ናቸው። ልቦቻቸው ከአንተ በመራቅ ነበልባሎች አልቀዋል፥ ለድምቀቶችህም መገለጽ በጉጉት ይጠባበቃሉ። ከስውር መንግሥትህ፥ ከማይታየው ግዛት፥ የጸጋህን አንጸባራቂ ክብር ግለጽላቸው፥

እንዲሁም በችሮታህን ደማቅ ብርሃን ከለላ ሁንላቸው። በእያንዳንዱ ቅጽበት ከአንተ የመነጨ አዲስ ቡራኬ እና ችሮታም ግለጽ።

መለኮታዊ ሰጪ ሆይ! እኛ ደካሞች ነን አንተ ግን እጅግ ኃይል የተመላው ነህ። እኛ እንደ ጥቃቅን ጉንዳኖች ነን አንተ ግን የክብር ግዛት ንጉሥ ነህ። የእሳት ነበልባል ለማቀጣጠልና ድምቀቱን በስፋት ለማብራት እንችል ዘንድ፥ ጥንካሬን ለማሳየትና የተወሰነ ግልጋሎት ለመስጠት እንችል ዘንድ፥ ጸጋህን ስጠን ችሮታህንም አድለን። ለዚህ ጨለማው ምድር አብርኾትን እና ለዚህ በፍጥነት ለሚያልፍ የአቧራ ዓለም መንፈሳዊነትን ለማምጣት እንችል ዘንድ ፍቀድልን። ለደቂቃ እንዳናርፍ፥ ወይም በዚህ ዓለም አላፊ ነገሮች ራሳችንን እንዳናረክስ አስችለን። የመርሆ ድግስ ለማዘጋጀት፥ የፍቅር ስንኞችን በደም ስራችን እንድንቀርጽ፥ ፍርሃትና ስጋትን ወደኋላ እንድንተው፥ አልፎም እንደ ፍሬያማ ዛፎች እንድንሆን፥ በዚህ አላፊ ጠፊ ዓለም የሰው ልጅ ፍጹምነቶች እንዲታዩ ለማድረግ አስችለን። በእውነቱ አንተ ፍጹም ጸጋ የተመላው፥ እጅግ በጣም ሩህሩሁ፥ ምንጊዜም ይቅር ባዩ፥ መሃሪው ነህ።

20

እርሱ ንዑዱነው።

ጌታዬ፥ ንጉሴ፥ መሪዬ፥ እንዲሁም አለኝታዬ ሆይ! በአንደበቴ፥ በልቤ፥ እና በነፍሴ እንዲህ በማለት አንተን እጠራለሁ፦ ይህን የአንተ አገልጋይ በጥበቃህ ካባ፥ በማይረታው እርዳታህ ሸፍን በመከላከያህም የብረት ልብስ አልብሰው። በሕዝብህ መካከል አንተን እንዲያወሳ እና መልካም ባህርያትህን እንዲያወድስ እርዳው፥ እንዲሁም አንድነትህንና ቅድስናህን ለማከበር በሚደረግ እያንዳንዱ ጉባኤ ክብርህንና ውዳሴህን እንዲያሰማ አንደበቱን አፍታታ። በእውነቱ አንተ ኃያሉ፥ ኃይል የተመላው፥ ንዑዱ፥ በገዛ ራሱ ነዋሪው ነህ።

21

ሩህሩህ ጌታዬ ሆይ! አንተ የልቤና የነፍሴ እሾት ሆይ! ለወዳጆችህ የፍቅራዊ ደግነትህን ስጣቸው፥ የማያበቃ ምህረትህንም አድላቸው። ለጽኑ አፍቃሪዎችህ መጽናኛ፥ ለእነዚያ አንተን ለሚናፍቁትም ጓደኛ፥ አጽናኝ፥ እና አፍቃሪ ወዳጅ ሁንላቸው። ልቦቻቸው በፍቅርህ እሳት ተጋግሟል፥ ነፍሶቻቸውም ላንተ ባላቸው ጽናት ነበልባል ጋይቷል። እያንዳንዳቸው ሕይወታቸውን በፈቃደኝነት

አሳልፈው ለመስጠት እንዲችሉ ወደ ፍቅርህ መስዋዕት ሥፍራ መገስገስ ናፍቀዋል።

መለኮታዊ ሰጪ ሆይ! ችሮታህን አድላቸው፥ በቀጥተኛው መንገድ ምራቸው፥ መንፈሳዊ ድል ለመጎናጸፍ እንዲችሉ እርዳቸው፥ መንግሥት ሰማያዊ ስጦታዎችም አጎናጽፋቸው። ጌታ ሆይ በችሮታህና በጸጋህ እርዳቸው፥ ብሩህ ፊቶቻቸውን ለዕውቀትህ እራሳቸውን ባስገዙ ጉባኤዎች ውስጥ የመርሆ መብራቶች፥ እንዲሁም ቅዱሳን ቃላትህ በሚተነተኑበት ስብሰባዎች ውስጥ የመንግሥት ሰማያዊ ችሮታህ ምልክቶች እንዲሆኑ እርዳቸው። በእውነቱ አንተ ምህረት የተመላው፥ ፍጹም ጸጋ የተመላው፥ እርዳታው በሁሉም ሰዎች የሚለመነው ነህ።

22

እርሱ ንዑዱ፣ እጅግ በጣም አንጽባራቂው ነው።

መለኮታዊ ሰጪ ሆይ፥ ይቅር ባይ ጌታ ሆይ! የአንተን ውዳሴ በተገቢ ሁኔታ ላዜም ወይንም በበቂ ሁኔታ ላመልክህና ላሞግስህ እንዴት እችላለሁ? በምንም አንደበት አንተን መግለጽ ከስህተት ውጭ ምንም

ሊሆን አይችልም፥ በምንም ብዕር አንተን በጽሑፍ ለመግለጽ ይህን የማይደፈር ሥራ መሞከር የከንቱነት ማስረጃ ነው። ምላስ ከንጥረ ነግሮች የተዋቀረ መሳሪያ ብቻ ነው፥ ድምጽና ንግግርም በአጋጣሚ ከተገኙ ባህርያት ውጭ ምንም አይደሉም። ታዲያ የእርሱን ምንም አቻም ሆነ ተመሳሳይ የሌለውን ምስጋና፥ በምድራዊ የድምጽ መሳሪያ እንዴት ላወድስ እችላለሁ? መናገር የምችለው ሆነ የምፈልገው ነገር ሁሉ በሰው ልጅ አእምሮ ተጨብጦ የተገደበ እና በሰው ልጅ ዓለም ተወስኖ የተከበበ ነው። የሰው ልጅ አስተሳሰብ የመለኮታዊ ቅድስናን ከፍተኛ የተራራ ጫፍ እንዴት ከፍ ሊል ይችላል፥ እንዲሁም የከንቱ ሃሳብ ሸረሪት የከንቱ ምናቦች ደካማ ድር በቅድስና ሱባኤዎች ላይ ከቶ እንዴት ሊያደራ ይችላል? ኃይል አልባነቴን ከማረጋገጥና ድክመቴን ከመናዘዝ በቀር ምንም ማድረግ አልችልም። በእውነቱ አንተ እርሱ ሁሉ ያለው፥ የማይደረስበት፥እርሱ ከእነዚያ መረዳት ከተቸራቸው የመገንዘብ ደረጃ በላይ ከመጠን በላይ ከፍ ያልክ ነህ።

23

መለኮታዊ ሰፊ ሆይ፥ አንተ ዘለዓለም ይቅር ባዩ ነህ! አንተ ኃያሉ አምላክ ሆይ፥ አንተ ሩህሩሁ ነህ! ይህን እጅግ የሚወደድ አገልጋይህ በክብርህ ጥላ ሥር እንዲኖር ፍቀድለት፥ ለዚህም ምስኪኑና ዝቅተኛው በምህረትህ ክልሎች ውስጥ እንዲበለጽግና እንዲያብብ እርዳው። ከቅርበትህ ጽዋ እንዲጠጣ ስጠው፥ ከተባረከው ዛፍም ጥላ ሥር እንዲኖር ፍቀድለት። ቅርበትህን የመቀዳጀት ክብር አጎናጽፈው፥ ዘለዓለማዊ ተድላና ደስታ ለግስው። የዚህን የተባረከ ነፍስ ቀሪ ዘመዶች የተወዳጅ አባታቸውን ፈለግ እንዲከተሉ፥ በሰዎች ሁሉ መካከል የእርሱን ባህሪና ጠባይ እንዲያሳዩ፥ መንገድህን እንዲከተሉ፥ የአንተን መልካም ደስታ እንዲሹ፥ እና ያንተን ውዳሴ እንዲናገሩ በጸጋህ እርዳቸው። አንተ ምንጊዜም አፍቃሪው አምላክ፥ የቸርነት ጌታ ነህ።

24

አንተ ተወዳዳሪ የሌለህ አምላክ ሆይ! እኛ ትሁታን አገልጋዮችህ ነን፥ አንተ ደግሞ ንዑዱ ነህ። እኛ ኃጢአትኞች ነን፣ አንተ ደግሞ ምንጊዜም ይቅር ባዩ ነህ። እኛ ምርኮኞች፥ ድሃና ዝቅተኛ ነን፥ አንተ ደግሞ መጠለያችንና ረዳታችን ነህ። እኛ እንደ ጥቃቅን ጉንዳኖች

ነን፥ አንተ ደግሞ በእጅግ ከፍተኛው መንግሥተ ሰማይ የነገስክ ግርማዊ ጌታ ነህ። ለግርማህ ምልክት ማሳያ እንዲሆን ጠብቀን፥ እንዲሁም ጥንቃቄህንና እርዳታህን አታጓድልብን። ጌታ ሆይ! ፈተናዎችህ በርግጥ ጥብቅ ናቸው፥ መከራዎችህም ከብረት የተሰሩ መሰርቶችን አፈራርሶ ሊጥል ይችላል። ጠብቀህ አቆየን አበርታንም፤ ልቦቻችንን በሐሴት ሙላ አስደስትልንም። የተቀደሰው መንበርህን ልክ እንደ አብዱል-ባሃ ለማገልገል በጸጋህ እርዳን።

25

እርሱ አምላክ ነው።

አምላክ፥ አምላኬ ሆይ! በፍጹም ዝቅተኝነትና የጋለ ስሜት፣ ትህትናና ራስን ማስገዛት፥ ከእሾቶች ሁሉ እጅግ የላቀ ዋጋ ያለውን እንድታድለኝ፥ ከተግባሮች ሁሉ እጅግ አስመስጋኝ የሆነውን ወስንልኝ፥ እንዲሁም ደማቅ ንጋትህ ሲቀድ ወደ ከለላ ሰጪ ጥላህ ለገሰገሱት እና በጥብቅ መሸሸጊያህና በኃያሉ ምሽግህ ውስጥ መጠለያ ለፈለገው ለዚህ ቤተሰብ ሁሉንም ክብርና ፍጹምነት፥ ገጽታና ውበት፥ ብልጽግናና ደህንነት እንድታዝለት፣ በአንደበቴና በልቤ፥ በመንፈሴና በነፍሴ፥ በአዕምሮዬና በሕሊናዬ እማጠንሃለሁ። በእርግጥ እነዚህ ነፍሶች

ጥሪህን አድምጠዋል፥ ወደ መንበርህ ቀርበዋል፥ በፍቅርህ እሳት ተቀጣጥለዋል፥ እንዲሁም በቅድስናህ ልዝብ ነፋሶች ተነሳስተዋል። በእምነትህ ግልጋሎት ጽኑዎች፥ በገጽህ ፊት ትሁታን፥ እንዲሁም በከለላ ሰጪ ጥላህ ሥር የተከበሩ ነበሩ። በህዝብህ መካከል የስምህ ተሸካሚ እና በአገልጋዮችህ መካከል አንተን የሚያወሱ በመሆን ይታወቃሉ።

አምላክ፥ አምላኬ ሆይ! በጥንታዊው ክብርህ ክፍ አድርጋቸው፥ በታላቅነት መንግሥትህ ውስጥ አክብራቸው፥ እንዲሁም በዚህ ታላቅ ቀን በችሮታዎችህ አስተናጋጆች አግዛቸው። ጌታ፥ አምላኬ ሆይ! ለፈርጀ ብዙ ችሮታዎችህ ፋኖስ መስተዋት እና የአፍቃሪ ደግነትህና ጸጋዎች አሰራጮች መሆን እንዲችሉ ሰንደቃቸውን ወደላይ ከፍ አርገው፥ የጥበቃህን ሰፊ ድርኻ አድላቸው፥ ምልክቶቻቸውን በስፋት አሰራጭ፥ እንዲሁም ብሩህነታቸውን ከፍ አድርግ።

ጌታ፥ አምላኬ ሆይ! በብቸኝነታቸው ወዳጆቸው ሁን፥ በሐዘናቸውም ጊዜ በእርዳታህ ክበባቸው። መጸሐፍህን ለእነርሱ አውርሳቸው የስጦታዎችህንና የልግስናዎችህን ሙሉ መጠን አድላቸው። በእውነቱ አንተ ኃያሉ፥ ኃይል የተመላው፥ ቸሩ፥ ጸጋ የተመላው፥ በርግጥም አንተ መሃሪው፥ ሩህሩሁ ነህና።

26

አቤቱ ጌታዬ በፀጋ ሃብታም የሆንክ፣ ግርማ ሞገስህ ሙሉ፣
ውስጣዊ ልቤንና ነፍሴን፣ እውቀትህ አቅፎ መጠቅለሉ!

በንጋት የነፍሴ መጽናኛ ማንም ሳይሆን አንተ፤
ጉዳቴንና ሐዘኔን አዋቂ ማንም ሳይሆን አንተ።

ልብ ላፍታ ያህል ያንተን መወሳት ብታውቅ፥
ከአንተ ብቻ የናፍቆት ህመም ሌላ ወዳጅ አታውቅ።

ለአንተ የማያቃስት ልብ የጠወለገ ይሁን፥
ለአንተም የማያነባ ዓይን ይሻለዋል ዓይነ ስውር ቢሆን።

የኃይል ጌታ ሆይ፥ በእጅግ ጥልቅ ሐዘኔ ሁሉ ጊዜያት፥
ደማቅ ብርሃንን ለማግኘት ልቤ የአንተ ትውስታ ነበራት።

vበችሮታህ አማካይነት መንፈስህን በውስጤ ተነፍስብኝ፥
ምናልባት ፈጽሞ ያልነበረው ለዘላለም ቢሆንልኝ።

ችሎታችንንና እርባናችንን አትመለከት፥
የቸርነት ጌታ ሆይ፥ ባይሆን አንተ የምታፈሰውን ውበት።

በረራችው ዝግተኛ በሆነው በእነዚህ ክንፉ ሰባራ ወፎች
ከፍቅራዊ ምህረትህ ለግሳቸው አዲስ ክንፎች።